ቀን፡ ነሐሴ 25 ቀን 2004 ዓ.ም. (August 31, 2012)

# የትብብር ጥሪ ለያ ትውልድ ወገኖች በያሉበት

## ጉዳዩ ፡ የከፍተኛ 15 ቀይሽብር ተዋንያን ከፍያለው ዓለሙ

የከበረ ሰላምታችንን በቅድሚያ እናቀርባለን።

ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት ተጀምሮ የነበረው በከፍተኛ 15 የቀይ ሽብር ተዋንያን ቁንጮ ከፍያለው ዓለሙ ጉዳይ የመጀመሪያ እልባት አግኝቷል። ነሐሴ 18 ቀን 2004 ዓ.ም. (August 24, 2012) ከፍያለው ዓለሙ በሰሜን አሜሪካ ዴንቨር ኮሎራዶ የአሜሪካን ደህንነት ኃይሎች ቁጥጥር ሥር በመዋል ወደ እስር ቤት ገብቷል። የያ ትውልድ አባላትና የቀይሽብር ቀጥተኛ ተጠቂ ወገኖችና ቤተሰቦች በመላ እንኳን ደስ አላችሁ።

ወገኖች፡ ይህ በአድራጎቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለት አረመኔ ግለሰብ፡ በትዕቢት ያፈሰሰው የንጹሃን ወንድምና እህቶቻችን ደም፤ ዛሬ ከ34 ዓመት በኋላ ተፋራጅና ተሚጋች በማግኘት አንዱን ወንጀለኛ ለፍርድ ሊያቀርብ ተዘጋጅቷል። የያ ትውልድ ሰማዕታትን ጨምሮ የከፍተኛ 15ቶቹ ብርዬ ሀ/ማርያም፣ ክፍሌ ቁስ፣ ታደሰ ቢፍቱ፣ ግዛው ወረሳ፣ አፈሳ በቀለ፣ በዛ ገ/ሕይወት፣ አሸናፊ በቀለ፣ አሰለፈች፣ ዮሐንስ ስዩም፣ ዳንኤል አንጋጋው ወዘተ እና በርካታ ወጣቶች ደም ምንጊዜም ቢሆን ተፋራጅ እንዳለው እንረዳለን። የበርካታ ወጣቶችንና ጎልማሶችን ደም እንደውሃ አፍስሦ ምንም እንዳልሰሩ አድፍጦ መቀመጥና ይባስ ብሎ ያንን ትውልድ ተጠያቂ ለማድረግ የሚደረገው ሩጫና ታሪክ ብረዛ ተከላካይና ሀቁን አስረጂ ወገን እንዳለው ጥርጣሬ የሚገባን አይመስለንም። ጊዜው ምን ቢርቅ ታሪካችን ተዳፍኖ እንደማይቀመጥና ለትውልድ እንደሚተላለፍ የምናደርገው ጥረት ፍሬ እንደሚያሳይ በያትውልድ ስም እያደረግን ያለው እንቅስቃሴ ውጤት መስካሪ ነው።

የከፍተኛ 15ን ቀይ ሽብር ተዋንያን ከፍያለው አለሙ ያለበት ቦታ ከታወቀ ጀምሮ ጉዳዩን በመከታተል ሙሉ ትብብርና ድጋፍ ላደረጋችሁ ሁላ ልናመሰግን እንወዳለን። በተለይ ከፍያለው ዓለሙ የዛሬ 34 ዓመት የሰራውን ወንጀል የምታውቁትንና ያያችሁትን ለመመስከር ምንም ሳታወላውሉ ፈቃደኛ በመሆን ለተባበራችሁ ዛሬ ከፍያለው ዓለሙ ወደ እስር እንዲወረወር ያበረከታችሁት አስተዋጽዎ ውጤት ነውና በሰማህታት ወንድምና እህቶቻችን ስም ምስጋና እናቀርባለን። በቀጣይነትም ለሚካሄደው የፍርድ ሂደትም ሆነ ማንኛውም ጥያቄ አሁንም የሁሉንም ተባባሪነት ይጠይቃልና በጋራ በመተባበር ጉዳዩን ከዳር እናደርሰው ዘንድ በትህትና እንጠይቃለን።

ስለ ከከፍያለው ዓለሙ መያዝ በ Agust 31, 2012 የዴንቨር Local News, 9News ዘግቧል። በከፍያለው ዓለሙ የፍርድ ሂደት በአፋጣኝ እልባት ያገኝ ዘንድና ጉዳዩ ይበልጥ ትኩረት ይሰጠው ዘንድ የያ ትውልድ ወገኖች በሙሉ ተባባሪነታችሁና ድጋፋችሁ አስፈላጊ

መሆኑን አምነንበታል። በመሆኑም የከፍያለው መያዝ ዜና በወጣበት ድረ ገጽ 9News.com በመግባት ወይም ቀጥሎ ባለው Link በመጠቀም በአሜሪካን መንግስት ለተወሰደው እርምጃ አጠር ያለ ድጋፋችሁንንና አስተያየታችሁን በአስተያየት መስጫው ሳጥን ወይም በኢሜል jace.larson@9News.com በመስጠት ትብብር ታደርጉ ዘንድ በሰማዕታት ወገኖቻችን ስም እንጠይቃለን።

በ1970 ዎቹ የደርግ ቀይሽብር ተዋንያን ጉዳይ የሁላችንም የያ ትውልድ አባላትና ቤተሰቦች የጋራ ኃላፊነት ነው ብለን እናምናለን። በመሆኑም በየቦታው አድፍጠው የተቀመጡትን በደም የተነከሩ ወንጀለኞች ቢያንስ ሊታወቁ የሚገባቸው በመሆኑ የጉዳዩ ባለቤት ሁላችንም ነንና፤ ድጋፍና ትብብራችን ለግለሰቦችና ለተወሰኑ አካላት ሳይሆን ለሚነሳውና ለተነሳው ጉዳይ መሆኑን በማገናዘብ ድምጻችንን በጋራ እናሰማ እንላለን።

ዜናውን ከታች በአለው Link በመጠቀም ካደመጣችሁ በኋላ ከ Video መመልከቻው ከላይ በስተቀኝ ያለውን comment በመጫን በፈለጋችሁት ስም የድጋፍ ትብብራችሁንና አስተያየታችሁን በመስጠት በዚህ ጉዳይ ያለንን ትብብር በማሳየት በቀጣይነት አድፍጠው የተቀመጡ የቀይ ሽብር ተዋንያን ከያሉበት በማውጣት ሕዝብ እንዲያውቃቸው ማድረግ ይጠበቅብናልና እንተባበር።

http://www.9news.com/news/article/286267/42/Man-responsible-for-murder-torture-caught-in-Denver-area

የከፍተኛ 15 ወገኖችና ጉዳዩን በመከታተል ላይ ያሉ የያ ትውልድ ፈቃደኛ ወገኖች በጋራ።

እናመሰግናለን